በመሻር አስቀድመን መግለጫ መስጠት አለብን በማለት በተቃራኒው ክርክር በማቅረብ በአንድነት ለመስራት የተጀመረው መንገድ ለማጠናቀቅ ጥቂት እርምጃዎች እንደቀሩት እንድስተጓጎል ሆኖአል::

**SNLO ለምን ዉስጣዊና ዉጫዊ አሰራሮች ቀድመዉ እንድሰሩ ጠየቀ**

1ኛ/ እንድስተካከሉ የተጠየቁ ነጥቦች ለድርጅቱም ሆነ ለአመራሩና ለአባላቱ ለጋራ ጥንካሬና ግልጾ"ነት የሚረዱ ከመሆናቸው ባሻገር የማንንም ግለሰብ ወይም ቡድን የግል ጥቅም የማይነኩና ማንንም የማያስከርፉ በመሆናቸው 2ኛ/ ባለንበት 21ኛው ክፍለ ዘመን እንካን 5.5 ሚሊዮን ሲዳማን የሚወክል ድርጅት ይቅርና በሁለት ግለሰቦች መካከልም ግልጽ የሆነ የጋራ ዉል ስለሚያስፈልግ 3ኛ/ ግልጽ የሆነ አሰራርና ተጠያቂነትን ለማስፈን 4ኛ/ ዉስጣዊ አደረጃጀቱን ዘመናዊ ለማድረግ 5ኛ/ ማንኛዉም እንቅስቃሴ የሲዳማን ጥቅም የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ 6ኛ/ ከSLF ድርጅታዊ አሰራርና አደረጃጀትም ያስተዋልናቸዉ የሚከተሉ ችግሮችም ስላሉ ጭምር ነዉ::እንደሚታወቀዉ ከተለያዩ አጋር ድርጅቶችና ወገኖች በሚያገኛቸዉ ድጋፎችና ባለዉ እዉቅናና በሚሰጣቸዉ መግለጫዎች ለዉጫዊ አካል በጣም የተጠናከረ ድርጅታዊ እንቅስቃሴ ያለዉ ቢመስልም ለሲዳማና ድርጅቱን በቅርበት ለሚከታተል አካል መስተካከል የሚገባቸዉ ዉስጣዊ ችግሮች እንዳሉ መረዳት ይቻላል:: አንዳንዶቹን ለማንሳት ያህል 6.1/ ፖለቲካዊ ፕሮግራሙ አሁን ሲዳማ ዉስጥ ያለዉንና ብሔራዊና አለም አቀፋዊ የፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ እድገትን ባገናዘበ መልኩ የተሻሻለ ያለመሆኑ 6.2/ ድርጅታዊ መዋቅሩም የሰፋና ሁሉንም ያካተተ ያለመሆኑ 6.3/ ዉስጣዊ የአባላት ደንብና አሰራሩም ስርአትን የተከተለ አይመስልም 6.4/ የድርጅቱ ሊቀ መንበር አዳዲስ አባላትን ለመሳብና ለማሰራት ፍቃደኛነቱ አናሳ በመሆኑ ድርጅቱ ከተቋቋመበትና ጊዜና ከሚያገኘዉ ድጋፍ አንፃር በዉስጡ ያሉ አባላት የለም ማለት ያስችላል:: የሀገር ዉስጡን ትተን በዉጭ ለዚያዉም በቅርቡ ያሉትን በርካታ የሲዳማን ዜጎች ለማቅረብ አለመቻሉ በግልጽ ይታያል:: 6.5/ ኮሚቴያዊ አሰራር አይታይም:: በቋሚነት ከሚታወቀዉ የሊቀመንበርና የምክትል ኃላፍነት በስተቀር ሁሉም ሥራ የሚሰራዉ በዋናዉ ብቻ ነዉ:: 6.6/ በድርጅቱ ዉስጥ ከላይ እንደተጠቀሰዉ ኮሚቴያዊና ዘመናዊ አሰራር ባለመኖሩ ከፍተኛ የሆነ የፋይናንስ አጠቃቀም ችግር እንዳለ ለጥቅም ብለዉ ሊቀመንበሩን ከተጠጉና ሲፈልጋቸዉም አባል ነን የሚሉ ግለሰቦች ጭምርና የዉጭ ተመልካቾችም የሚመሰክሩት ጉዳይ ነዉ:: 6.7/ ግልጽ የሆነ የሥራ ድርሻና ኃላፍነት ስለሌለ አመራር ሰጭና አመራር ተቀባይ ተለይቶ አይታወቅም:: ሊቀ መንበሩ ያለዉን ሌላዉ ይሽርና ግለሰቡ በመሰለዉ ጊዜ የፈለገዉን እርምጃ ይወስዳል:: 6.8/ እርስ በርስ መተማመን የለም:: አንዱ ሌላዉን ለመጣልና ኃላፍ ለመሆን ከድርጅቱ ዉጭ ያሉትን በተለያዩ ሁኔታዎች እየሰበከ የራሱን ፕሮፖጋንዳ ሲያካሂድ ይስተዋላል:: 6.9/ አባል ነዉ በተባለዉ ግለሰብ ላይም የማባረርና የመመለስ እርምጃም በአንድ ግለሰብ በሰአታት ዉስጥ ጊዜ ብቻ ይጠናቀቃል:: 6.10/ ድርጅቱ የራሱ የሆነ የሥራ እቅድና ፕሮግራም ያለዉ አይመስልም:: ሁኔታዎች ሲመቻቹና ዉጫዊ አካል ለአጋርነቱ ተጨንቆ በሚያደርገዉ ግፍት ብቻ እንቅስቃሴ ሲደረግ ይታያል:: 6.11/ ገንቢ የሆነ የሥራና የእቅድ ግምገማ የለም:: ወያኔያዊ የሆነ የእርስ በርስ መባላት ካልሆነ በስተቀር:: 6.12/ ሊቀ መንበሩና በሌላ ቦታ ካሉ ምክትልና አመራር በስተቀር በዉስጡ አለን የሚሉ እያራመዱት ያለዉ የራሳቸዉን የወደፍት ኑሮ አጀንዳ ማመቻቸት እንጂ የሲዳማ ሕዝብ ትግል አላማቸዉና አጀንዳቸዉ እንዳልሆነ ከቆይታ ጊዜያቸዉ አንፃር ያደረጉትና በማድረግ ላይ ያሉት ግልጽ ተግባራቸዉ ምስክር ነዉ:: 6.13/ ድርጅቱ በተለያዩ ጊዜያት የሚሰጣቸዉ መግለጫዎች ቆሜለታለሁ ከሚለዉ አላማና ከሲዳማ ሕዝብ ጥቅም ጋር የሚጋጭ ከመሆኑም ባሻገር የሚሰጠዉ መግለጫ ሳይገመገምና በድርጅቱ ያልተከናወኑ ተግባራትን በማስተላለፍ የወያኔዉ ሥርአት በንጹሃን ዜጎች ላይ ጅምላ እስራትና ግድያ እንድፈጽም አስተዋጽኦ ማድረጉ::

ስለሆነም ነዉ ከላይ እንደተመለከተዉ SNLO ቀድመን በነዚህ ዉሰጣዊና ዉጫዊ አሰራሮች ላይ ግልጽ የሆነ አቅጣጫ እንድኖር የጠየቀዉ::

**የአብሮ መስራቱ ጥረት መክሸፍ**

ከላይ በዝርዝር እንደተቀመጠዉ ብዙ መንገድ በመጓዝ በብዙ አጨቃጫቂ ሁኔታዎች ላይ ከስምምነት ተደርሶ እያለ የወደፍቱን ሂደት አስተካክለን እንሂድ በሚለዉ የSLF ሊቀመንበር የተስማማበትን ዉሳኔ በመሻሩ ዉይይቱ ተቋርጣል::

**ዉይይቱን ለመቀጠል በSNLO የተቀመጡ አማራጮች**

SNLO ዉይይቱን ያቋረጠዉ ከስምምነት ላይ የተደረሱ ነጥቦች በSLF በኩል በተደጋጋሚ በመጣሳቸዉና ግልጽና ዘመናዊ የሆነ አሰራር እንድኖር ባለመፈለጉና መተማማን በመጥፋቱ ቢሆንም ሌላ 3ኛ አካል ማለትም በቅድሚያ የብሔሩ አባላት የሆኑ ይህም ካልሆነ ደግሞ የትግል አጋር የሆኑ ድርጅቶችና ወገኖች በግልም ይሁን በጋራ በተገኙበት ከSLF ጋር ብቻ ሳይሆን ከSLM እና ሌሎች የሲዳማ ድርጅቶችም ካሉ ዉይይት ለማድረግና በጋራ ለመንቀሳቀስ እንደሚፈልግ አቋሙን ግልጽ ያደርጋል::